# Legacy International Spiritual Ministry 2024 GC Annual Report




**Legacy International Spiritual Ministry c/o P.O.Box 17979**

**Cell # 251 930 651943**

**Act: #: Berhan Bank 2600010008458; Awash Bank 013521121036500; CBE 1000312358337**


***ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!***

***ጉዳዩ፡* እአአ 2024 የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት ዓመታዊ ሪፖርት ባጭሩ**

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2017 በይፋ ሥራዉን ከጀመረ ስምንተኛ ዓመቱን አጠቃልሎ ዘጠነኛዉን ተያይዟል፡፡ ስምንተኛ ዉን ዓመት ሲያጠቃልል በሥራ አመራር ቦርዱና በጠቅላላ ጉባዔ እአአ የ2024 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴና የኦዲት ሪፖርትን በማድመጥና በማጽደቅ ነበር፡፡ የበጎ ፈቃደኞች (በተለይ ወጣት አሠልጣኞች)፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በሀብታቸው ከአገልግሎቱ ጎን የመቆም ሂደት አሁንም ቀጥሏል፡፡ የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉ ማለትም ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በተለያዩ አካባቢዎች የግንባር ሥልጠናን የመስጠት ሥራ በስምንተኛዉ ዓመት ከታቀደዉ አንጻር ሲታይ የ161% ክንዉን ዉጤት ታይቶበታል፡፡ ይህ ዉጤት ካለፈዉ ዓመት ጋር ሲነጻጸር ዘቅተኛ ቢመስልም ከታቀደዉ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነዉ፣ በመሆኑም፣ እግዚአብሔር ስላበዛልን ፀጋ እናመሰግነዋለን፡፡ በዚህ በስምንተኛ ዓመት ማጠቃለያ ቀደም ብሎና ባለፈዉ ዓመት ኃላፊነት የወሰዱ ቦርድ አባላት አገልግሎታቸዉን በትጋት ፈጽመዋል፡፡ በትዕግሥትና በትጋት እያገለገሉ ስለሆነ ጌታ ይባርካቸዉ፡፡ ሌላዉ ስምንተኛ ዓመቱን ልዩ የሚያደርገዉ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ከ**ሰንበት በኋላ ወደ ተሻለ ፕሮፋይል መዘርጋት መጀመሩ ነዉ፤** ለዚህም ጌታ ይባረክ፡፡

**ክፍል አንድ - የመረብ ግኑኝነት እንቅስቃሴዎች**

**1.1 ከኢቲሲ በተገኘዉ ግብዣ፣ በእንግዳ አስተማሪነት** (Guest Lecturer) ለግማሽ ቀን ማርች 9፣ 2024 በእምነት ዕድገት (Faith Development) ላይ ከ16 ለማያንሱ ተማሪዎች ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

**1.2 የጥምረቶች ግኑኝነት**

**ሀ.** በዎርል ቪዥን የተደገፉ የፋይናንስ ጨምሮ፣ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን ለመካፈል ተችሏል፡፡

**ለ. የልጆች አገልግሎቶች ጥምረት ጥምረት (CAG & VAE)*** ኃላፊነት ላይ የሚገኙ አንዳንድ የጥምረቱ አባል ድርጅቶች መሪዎች/ተወካዮች እአአ ኖቬምበር 21 እና 22፣ 2024 በብሾፍቱ/ባቦ ጋያ መልካም መንፈሳዊ ሪቲሪት ጊዜ አሳልፈናል፡፡ የእርስ በርስን ግኑኝነትን ለማጠናከር ጠቃሚ ነበር፡፡



**ሥዕል 1:** የኢቲሲ ተማሪዎች

* **CAG = Christian Alliance for Generation; VAE)= Voice Alli-**



**ሥዕል 2:** የልጆች አገልግሎቶች ጥምረት ጥምረት (CAG & VAE) መሪዎች ህብረት ጊዜ በደብረ ዘይት (ብሾፍቱ)

**2.1.2 የዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ወጣቶች ሥልጠና፡-**

**መጋቢት 7፣ 2016** (March 16, 2024) ቅዳሜ (ከሰዓት በፊትና በኋላ) በሶስት ርዕሶች ላይ ሥልጠና ተስጥቷል፣ እነርሱም ሀ) የወጣቶች ተግዳሮቶች (በዶር ተስፋዬ አለሙ) ከሰዓት በፊት፣ ለ) በአእምሮ መንፈስ መታደስ ላይ ያተኮረ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች) እና ሐ) የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር ናቸዉ። **የተሳታፊዎች ብዛት 62 ነበር።**



**ሥዕል 3፡** የዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ወጣት/ታዳጊ ሠልጣኞች

**2.1.4 ድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የወጣቶች ሥልጠና**

ይህ ሥልጠና የተካሄደዉ ህዳር 1፣2017 (November10፣2024) እሁድ ከሰዓት በኋላ ሲሆን፣ በሁለት ርዕሶች ላይ ነዉ፣ እነርሱም ሀ) በአእምሮ መንፈስ መታደስ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች) እና ለ) የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር ናቸዉ። በሁለቱም ርዕሶች ላይ በአንድ ክፍለ ጊዜ የተካፈሉት በከፍተኛዉ ቁጥር **30 ወጣቶች** ናቸዉ።

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

## ክፍል ሁለት፡ - በሌጋሲ የተሰጡ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች

### 2.1 የወጣቶች ግንባር ሥልጠና

### 2.1.1 መሠረታዊ ዳሰሳ

በወጣቶች የግል ጊዜ ከጌታ ጋር ግንባር ሥልጠና ቅድመ እና ድህረ ዳሰሳ በተደረገዉ በታዎች የተገኘዉ ለዉጥ ዉጤት በዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ወጣቶች 26%፣ በድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ወጣቶች 23%፣ በድሬዳዋ ዩኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች 20%፣ በሀረማያ ዩኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች 58%፣ በደምቢ ዶሎ ቁጥር ሁለት ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ አስተባባሪነት በተዘጋጀዉ ሥልጠና ላይ የደምቢ ዶሎ ዩኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች 48%፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወጣቶች በተሳፉበት ሥልጠና 71%፣ ነዉ። ይህ የሚያመለክተዉ ቀደም ብሎ የጥሞና ጊዜ ያልነበራቸዉ ወጣቶች ከሥልጠናዉ በኋላ ይህን ለመለማመድ መወሰናቸዉን የሚያሳይ ነዉ። እግዚአብሔር ይመስገን።

### 2.1.3 በጀሞ ሙሉ ወንጌል የወጣቶች ሥልጠና

ይህ የተደረገዉ በተከታታይ ሳምንታት ነዉ። የተካሄደዉ በሁለት ቅዳሜ ምሽቶች ላይ ነዉ ። ይኸዉም ግንቦት 10፣ 2016 (May 18, 2024) እና ግንቦት 17፣ 2016 (May 25, 2024) ነዉ። የሥልጠናዉ ትኩረት የነበረዉ ትዳርን በመልካም መጀመርና መጨረስ ሲሆን፣ የተካፈሉት ወጣቶች **በከፍተኛዉ ቁጥር 56** ናቸዉ።



**ሥዕል 4:** የጀሞ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ወጣት ሠልጣኞች



**ሥዕል 5፡** የድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ ወጣቶች

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ።**

**2.1.6 ሃረማያ ዩኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ሥልጠና፤** በእግዚአብሔር እርዳታ ባቲ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ለተሰባሰቡ የሃረማያ ዩኒቬርስቲ ተማሪዎች የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር በሚል ርዕስ ላይ ሮብ ምሽት ህዳር 4፣ 2017 (November 13፣ 2024) ሥልጠና ተስጥቷል። ተሳታፊዎች **69 ተማሪዎች** ነበሩ።



***ሥዕል* 7፡ *የሃረማያ*** ዩኒቬርሰቲ ሠልጣኝ ወጣት ተማሪዎች

**2.1.7 በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያን ተማሪዎች ሥልጠና**
በሙሉ ወንጌል አስተባባሪነት የሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያን ተማሪዎች ሥልጠና የተሰጠዉ የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር በሚል ርዕስ ላይ ሲሆን፣ የተከናወነዉ ታህሣሥ 9፣ 2017 (December 18, 2024) ሮብ ከሰዓት በኋላ ነዉ። ተሳታፊዎች **301 ተማሪዎች** ነበሩ።



***ሥዕል* 8.1 - በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ አስተባባሪነት የደምቢ ዶሎ የኒቬርስቲ ሠልጣኝ ክርስቲያን ተማሪዎች**

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

**2.1.5 ድሬ ዳዋ የኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ሥልጠና፣**
በእግዚአብሔር እርዳታ በሌጋሲ ጥረት በተደረገዉ የማስተባበር ሥራ ዩኒቬርስቲ አከባቢ በሚገኘዉ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ለተሰባሰቡ ተማሪዎች የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር በሚል ርዕስ ላይ ሰኞ ምሽት ህዳር 2፣ 2017 (November 11፣ 2024) ሥልጠና ተስጥቷል። ተሳታፊዎች **76 ተማሪዎች** ነበሩ።




***ሥዕል* 6፡- *የድሬዳዋ*** ዩኒቬርሰቲ ሠልጣኝ ወጣት ተማሪዎች

**2.1.8 የደምቢ ዶሎ የኒቬርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ሥልጠና፡-**
በሙሉ ወንጌል አስተባባሪነት ይህ ሥልጠና ታህሣሥ 12፤ 2017 (December 21፣ 2024) ቅዳሜ ከሰዓት በፊት፣ ዩኒቬርስቲ አቅራቢያ በሚገኘዉ ሙሉ ወንጌል ሰብከት ጣቢያ ላይ፣ በሁለት ርዕሶች ላይ ተካሂዷል። እነርሱም፣ ሀ) በአእምሮ መንፈስ መታደስ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች)፣ ለ) የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር ሥልጠና የሚሉ ናቸዉ። በሁለቱም ርዕሶች ላይ በአንድ ክፍለ ጊዜ የተካፈሉት ወጣቶች **85 ተማሪዎች** ናቸዉ።



***ሥዕል* 8..2 - በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ አስተባባሪነት የደምቢ ዶሎ የኒቬርስቲ ሠልጣኝ ክርስቲያን ተማሪዎች**

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

### 2.1.9 የደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ሥልጠና፡-

ይህ የተካሄደዉ ታህሣሥ 12 እና 13፤ 2017 (December 21 & 22፣ 2024) ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በሁለት ርዕሶች ላይ ተሰጥቷል፣ እነርሱም፣ ሀ) ወጣትነት፣ የወጣቶች ግዳሮቶችናመፍትሔሃሳቦች እና ለ) በአእምሮ መንፈስ መታደስ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች) ሐ) የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር ሥልጠና እሁድ ከሰዓት በኋላ፣ ናቸዉ፡፡ በሶስቱም ርዕሶች ላይ በሁለት ክፍለ ጊዜ (ቅዳሜ ከሰዓትና እሁድ ከሰዓት) የተካፈሉት **በድምሩ 331** ወጣቶች ናቸዉ፡፡



ሥዕል 9 - በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ ወጣቶች (በከፊል)



ሥዕል 10 - በለቡ (አአ) መኖርያ ቤት በነበረዉ ሳሜር ክምፕ ላይ የተሳተፉ ልጆች

### 2.1.10 የልጆች ሳሜር ካምፕ፡-

**2.1.10 የልጆች ሳሜር ካምፕ፡-** ይህ የተደረገዉ ከቤተዘመድ አካባቢ ስለዚህ ጉዳይ የመነጨዉን ሃሳብ እንደ ዕድል በመዉሰድ፣ ቀደም ብሎም በስልታዊ አቅድ ያለ መሆኑን በማጤንና አስፈላጊዉን ዝግጅት በማድረግ ነዉ። የልጆች ሳሜር ካምፑ የተካሄደዉ **ከሰኔ 24-26፣ 2026 (July 1-4, 2024)** በሌጋሲ ባለራዕዮች መኖርያ ቤት ሲሆን፣ የተሳፉት ልጆች የዕድሜ ክልል ከ4-22 የሚደርስ ነበር። ለአሠራር እንዲያመች ልጆቹን በሁለት ግሩፕ በመከፈል፣ እንደ የዕድሜያቸዉ አቅም ትምህርቶች መስጠት ተችሏል። የመኝታ ልብሶች ድጋፍና ምግብ ከወላጆቻቸዉ ተደርጎላቸዋል። ፕሮግራሙ ሰኞ ጧት ተጀምሮ የተጠናቀቀዉ ሮብ ሲሆን፣ ያም በአንድነት ሽርሽር በመዉጣት ነዉ። **የልጆቹ ቁጥር 18 ነበር።**



ሥዕል 11 - ዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ሠልጣኝ ወላጆች

## 2.2 የወላጆች ግንባር ሥልጠና

### 2.2 .1 ዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ የወላጆች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ መጋቢት 6፣ 2016 (March 15, 2024) ዐርብ ከሰዓት በኋላ ሲሆን፣ የቀረቡት ርዕሶች፡ የትዉልዶች ተግዳሮቶች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ፣ የወላጆች ከክፉ አምልጦ ማስመለጥ (ሰባቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች) የነበሩ ሲሆን ተሳፊዎች **32 ሰዎች** ናቸዉ። የተለያዩ የልጆች አስተዳደግ ልምምዶች በተመለከተ የታዳጊዎች ድራማም

### 2.2.2 ጀሞ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የወላጆች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ በሶስት ቅዳሜዎች ሲሆን፣ ይኸዉም ሰኔ 8፣ 15፣ 22፣ 2016 (June 15, 22, 29, 2024) ነበር፤የመጀመሪያዉ ቀን ትኩረት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ፣ ሁለተኛዉ ቀን ትኩረት ሰባቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች፣ በ11 የወላጅነት ነጥቦች ተጠቅልሎ፤ ሶስተኛዉ ቀን ትኩረት ጤናማ አመጋገብ (በዶ/ር አወቀ) የሚሉ ነበሩ። የየዕለቱ ታስቦ ሥልጠናዉን የተካፈሉ **36 ሰዎች** ናቸዉ።

ሥዕል 12 - ጀሞ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ ወላጆች



**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ**

**ነ ዉ።**

### 2.2.4 ድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወላጆች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ ጥቅምት 29 እና 30፣ 2017 (November 8 & 9፣ 2024) ነበር። የመጀመሪያዉ ቀን ትኩረት **መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ** ሲሆን ሁለተኛዉ ቀን ትኩረት ደግሞ **ትዉልድን አምልጦ ማስመለጥ** በሚል ርዕስ ላይ ነዉ። የተሳታፊዎች **ቁጥር በድምሩ 61 ሰዎች** ነበር።



**ሥዕል 13፡ -** ድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ ወላጆች

## 2.3 የመሪዎችና አገልጋዮች ግንባር ሥልጠናዎች

### 2.3.1 ዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ፣ የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ አገልግሎትና አገልጋይነት በሚሉ ርዕሶች ላይ **መጋቢት 5፣ 2016** (March 14, 2024) ሐሙስ ነዉ። በተካሄደዉ ሥልጠና የተካፈሉት **16 ሰዎች** ናቸዉ፤ የሥልጠናዉ ትኩረት እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳ ትዉልዱ ቸል እንዳይባል፣ በአገልጋይነት መንፈስ ተግቶ በመሥራት ትዉልድን የማስመለጥ አስፈላጊነት ላይ ነበር።

### 2.3.2 ድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ **በትዉልዶች ተግዳሮቶች፣ አገልግሎትና አገልጋይነት** በሚሉ ርዕሶች ላይ ነዉ። ጥቅምት 30፣ 2017 (November 9፣ 2024) ከሰዓት በፊት በተካሄደዉ ሥልጠና የተካፈሉት **26 ሰዎች** ናቸዉ፤ የሥልጠናዉ ትኩረት እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳና ትዉልዱ ቸል እንዳይባል፣ በአገልጋይነት መንፈስ ሆኖ፣ ተግቶ በመሥራት ትዉልድን የማስመለጥ አስፈላጊነት ላይ ነበር።

### 2.2.3 የቦሰተን ዲያሰፖራ ቤ/ክርስቲያን በአሜሪካ፤ የወላጆች ሥልጠና

**ይህ** የተከናወነዉ በዙም (Zoom) አምስት ጊዜ ሲሆን፣ እ.አ.አ ኦክቶቤር (October 3, 10, 17, 24, 31, 2014) በየሳምንቱ በአዲስ አበባ አቆጣጠር ሐሙስ ሐሙስ ጧት ሥልጠናዉን ኦንላይን (Online –Video) በማካሄድ ነው። የሥልጠናዉ ትኩረት ለአራት ሳምንታት **ትዉልድን አምልጦ ማስመለጥ** ሲሆን አንዱ ሳምንት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ (በእህት በላይነሽ) ነበር። በመሆኑም የእያንዳንዱ ሳምንት ተደምሮ በዙም

### 2.2.5 በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የወላጆች ሥልጠና

ይህ የተካሄደዉ ታህሣሥ 10 እና 11፤ 2017 (December 19 & 20፣ 2024) ነበር። የመጀመሪያዉ ቀን ሐሙስ ከሰዓት ትኩረት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ቀን (ዐርብ ከሰዓት በፊትና በኋላ) ትኩረት ደግሞ የትዉልዶች ተግዳሮቶች፣ ትዉልድን አምልጦ ማስመለጥ፣ ልጅን በዲሲፒሊን ማሳደግ፣ በሚል ርዕሶችና የልጆች አስተዳደግ ልምምዶች ድራማ፣ በታደጊዎች የተዘጋጀና የቀረበ ነበር። የሁለቱም ቀናት ተደማምሮ የተሳታፊዎች ቁጥር **264 ሰዎች** ነበር።



**ሥዕል 14፡ -** ደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ ወላጆች



**ሥዕል 15፡ - ድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ሠልጣኝ መሪዎችና አገልጋዮች (በከፊል)**

**2.3.3 ደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና**
ይህ የተሰጠዉ በትዉልዶች ተግዳሮቶች፣ አገልግሎትና አገልጋይነት በሚሉ ርዕሶች ላይ ነዉ። ታህሣሥ 10፣ 2017 (December 19, 2024) ሐሙስ ከሰዓት በፊት በተካሄደዉ ሥልጠና የተካፈሉት **87 ሰዎች** ናቸዉ፤ የሥልጠናዉ ትኩረት እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳና ትዉልዱ ቸል እንዳይባል፣ በአገልጋይነት መንፈስ ሆኖ፣ ተግቶ በመሥራት ትዉልድን የማስመለጥ አስፈላጊነት ላይ ነዉ።

**ክፍል ሶስት ፡ በእሁድ አምልኮ ላይ የነበረዉ ትዉልድን የማስመለጥ አገልግሎት**

**3.1 በዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ በእሁድ አምልኮ** ላይ ትዉልድን ማስመለጥ በተመለከተ አገልግሎት የተካሄደዉ መጋቢት 8፣ 2016 (March 17, 2024) ሆኖ፣ በትምህርታዊ ስብከት፣ ለወጣቶች 5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች እና የወላጅነት 11 ነጥቦች ቀርበዋል። በፕሮግራሙ ላይ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ በግምት **375 ሰዎች** ይሆናሉ።



**ሥዕል 16፡ - በዝዋይ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ በእሁድ አምልኮ ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች**

**3.2 ማራናታ ዲያስፖራ ቤተ ክርስቲያን በሳንዲያጎ (ካሊፎርኒያ-አሜሪካ)** ሁለት እሁድ አምልኮ ላይ ትዉልድን በማስመለጥ ረገድ መልእክቶች ተላልፈዋል። ቀናቱ August 4፣ 2024 (ሐምሌ 28፣ 2016) እና August 11, 2024 (ነሐሴ 5፣ 20216) ነበሩ። በሁለተኛዉ ቀን መጨረሻ ፕሮፌቲክ መልእክት የመጣዉ ህዝቡ ልጆችን ከማሳደግ አንጻር ራሱን መመርመር እንዳለበት የሚያመለክት ነበር፤ በሁለቱም እሁዶች በግምት በድምሩ ወደ **225 ሰዎች** መልእክቱን ሰምተዋል።

**3.3 መድኃነዓለም ዲያስፖራ ቤተክርስቲያን በሲያትል (አሜሪካ)፤** በእሁድ አምልኮ ላይ በተሰጠዉ አገልግሎት ትኩረቱ ትዉልድን የማስመለጥ ትምህርታዊ መልእክት ላይ ነበር። ይህ አገልግሎት በአንድ ቀን፤ August 25፣ 2024፣ ሁለት ካምፓሶች (ደቡብ ከሰዓት በፊት፣ ሰሜን - ከሰዓት በኋላ) ላይ ተከናዉኗል። ምዕመናኑ መልእክቶቹን በኢንተርኔት የመከታተል ዕድሉ ስለነበራቸዉ፣ በሁለት ክፍሎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በድምሩ መልእክቱን በግንባር በተለያየ ጊዜና ቦታ የተከታተሉ ወደ **950 ሰዎች** ይሆናሉ።

**3.4 በድሬ ዳዋ መሃል ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በእሁድ አምልኮ** ላይ ትዉልድን ማስመለጥ በተመለከተ አገልግሎት የተካሄደዉ ህዳር 1፣ 2017 (November 10፣ 2024) ነበር። በትምህርታዊ ስብከት መልክ ለወጣቶች 5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች ላይ ፣ የወላጅነት 11 ነጥቦች ቀርበዋል። በእሁድ አምልኮ ላይ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ በግምት **450 ሰዎች** ይሆናሉ።



**ሥዕል 17-** በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ በእሁድ አምልኮ ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች

**3.5 በደምቢ ዶሎ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ** በእሁድ አምልኮ ላይ ትዉልድን ማስመለጥ በተመለከተ አገልግሎት የተካሄደዉ ታህሣሥ 13፤ 2017 (December 22፣2024) ነበር። በትምህርታዊ ስብከት መልክ፣ ለወጣቶች 5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች፣የወላጅነት 11 ነጥቦች ቀርበዋል። እህት በላይነሽ መገርሣ እና ዶር ተስፋዬ አለሙም ስለትዉልዱ ያላቸዉን መልእክት ተራ በተራ፣ በእሁድ አምልኮ ላይ አስተላልፈዋል። በእሁድ አምልኮ ላይ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ ወደ **2300 ሰዎች** ይሆናሉ።

# ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

**ማስታወሻ፣** በሁሉም **7** ጣቢያዎች በተደረገዉ ሥልጠና የተካፋዮች **ቁጥር 1726** ሲሆን፣ በቀድሞ ሥልጠና ጉብኝት ዉቅት በ1 ጣቢያ የተገኙት **26** በመሆናቸዉ፣ **በ8ቱም** ጣቢዎች የነበሩ ተሳፊዎች ድምር **1752** ነዉ። በእሁድ አምልኮ ላይ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ ወደ **4425** እንደሆኑ በመገመቱ እአአ 2024 በጀት ዓመት የተደራሾች ድምር **6177** መሆኑ ታዉቋል።

# ኢ የ ሱ ስ  ጌ ታ  ነዉ።

**ክፍል አራት ፡ የቀድሞ ሥልጠና ጣቢያ ጉብኝትና የተገኘዉ ዉጤት**

**በላፍቶ ፉሪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርሰቲያን አስተባባሪነት ቀደም ብሎ የ**ወላጆች፣ ሥልጠና የተካሄደዉ ታህሳስ 5 እና 12፣ 2012 (**Dec 15 & 22 2019)** ሲሆን፣ ጉብኝት የተደረገዉ ደግሞ ሚያዝያ 23፣ 2016 (May 1, 2024) )ለግማሽ ቀን ነበር። የጉብኝቱ ዓላማ - ቀድሞ ስለተሰጠዉ ሥልጠና ግብረ መልስ ለማግኘትና በወቅቱ የትዉልዶች ተግዳሮቶች ላይ ሥልጠና ለመስጠት ነዉ። በጉብኝቱ ፕሮግራም ላይ የተሳተፉት **23 ወላጆች** ሲሆኑ፣ የቀደመዉን ሥልጠና ተካፍለዉ የነበሩ ወላጆች፣ **6** ናቸዉ። በተጨማሪም በቀጣይነት ትዉልድን ለማስመለጥ የሚረዳ ለሶስት ወር የሚያገለግል የወላጅነት መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ማቴሪያል በሌላ ጊዜ ተበርክቷል። ከግብረ መልሱም፣ በቀደመዉ ሆነ በቀኑ በተደረገዉ ሥልጠና የጠቀማቸዉን፣ የነበሩት ጠንካራና ደካማ ነጥቦች፣ እንዲሁም ሊሻሻሉ የሚገባቸዉና ለሌጋሲ አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ ገንቢ ሃሳቦችም ተሰብስበዉ ለመረጃነት ተይዘዋል። **ከቀደመዉ ሥልጠና አንድ ተጠቅመናል በማለት ግብረ መልስ የተሰጠዉ ሲጠቃለል -** ልጆች በእግዚአብሔር መንገድ እንዲሄዱ የወላጆች ሚና፣ በተለይ በመቅጣት ጊዜ መስማማት እጅግ ከፍተኛና ወሳኝ መሆኑን፣ ከልጆች ጋር አብሮ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና መፀለይ አስፈላጊነት፣ ልጆች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ስለመፀለይ የተሰማዉ ምሥክርነት ናቸዉ።

**ክፍል አምስት - እአአ 2024 የሂሳብ እንቅስቃሴና እአአ የ2025 በጀት ዕቅድ**

እአአ 2023 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት **ብር 773,860.00** (ሰባት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ ብር) የነበረ ሲሆን፣ አጠቃላይ ወጪ ብር 312,594.32 (ሶስት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና አራት ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም) ነበር፤ ይህም በኦዲቴር የተረጋገጠ ነዉ።
እአአ ለ2025 ዓም ለአገልግሎቱ የተያዘዉና በቦርድ ታይቶና በጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀዉ **ብር 1,102,600.00** ነዉ። ለተፈጻሚነቱ እንፀልይ፣

**ማጠቃለያ** ፣ ለዚህ አገልግሎት መሳካት ምክንያት፣ ከሁሉ በላይ ሊመሰገንና ከፍ ሊል የሚገባዉ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነዉ። በማይመቹ አካባቢዎች ስንንቀሳቀስ ሁሉ ጥበቃዉን ያበዛልን እርሱ ነዉና ክብር ለርሱ ይሁን። አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆምና ወደፊት እንዲሮጥ፣ አገልግሎቱን በመምራት በትጋት ለተንቀሳቀሳችሁ ቦርድ አባላት ፤ በቋሚነት ገንዘባችሁን በመለገስ ለተጋችሁ ደጋፊዎች፤ በበጎ ፈቃደኝነት ጊዜያችሁን ፣ ጉልበታችሁን በመስጠት ላገለገላችሁ ወገኖቸ ፣ በራችሁን በመክፈት በትብብር እንዲሠራ ለፈቀዳችሁ፣ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ ላላችሁ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህ ሪፖርት አማካይነት ተሰጥቶአችኋል።

እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና። ዕብራውያን 6:10፤

***እርስዎና ቤተሰብዎም ለዚህ አገልግሎት መሳካት በበዛልዎት ፀጋ የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ እንላለን።***

**መጨረሻ**